| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ዐምደኛ ፡ ድርሰት ፤ ጥርየታዊ ፡ ትንታኔ ። |
| ርእስ ፤ | "ምጥራይ ፡ ወይም ፡ ጥርየታዊ ፡ ሥርዐት ። " |
| ደራሲ ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው |
| ዕለት ፤ | ሚያዝያ ፡ 2011 |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ፥ ቊ.2011.001 |
| ማስታወሻ ፤ | ተከታታይ ፡ ዐምድ ። |
| ማሳሰቢያ ፤ | |



# ጥርየታዊ ፡ ትንታኔ ።

Economic Analysis | Analyse économique

# ምጥራይ ፡ ወይም ፡ ጥርየታዊ ፡ ሥርዐት ።

## ጥርጊያ ፡ መንገድ ።

**ጥርየታዊ ፡ ትንታኔ** ፡ በሚል ፡ በዚህ ፡ ዐምዳችን ፥ **ጥርየታዊ** ፡ ወይም ፡ *"ኤኮኖሚያዊ"* ፡ በ'ኾነ ፡ ጕዳይ ፡ የባለሚያ ፡ ትንታኔ ፡ ይቀርብበታል ። ለርእሰ ፡ ጕዳዩ ፡ ጥርጊያ ፡ መንገድ ፡ እንዲ'ኾነን ፥ ከቃላት ፡ ፍች ፡ አንሥቶ ፡ እስከትንታኔው ፡ ስልት ፡ ያሉትን ፡ ግንዛቤዎች ፡ በሰብሳቢ ፡ አገላለጥ ፡ ለአንባቢው ፡ በመተንተን ፡ እንዠምራለን ።

በእንግሊዝኛ ፡ **"economy"** ፡ የተባለው ፡ ቃል ፡ ከግሪክኛው ፡ **"oiko-nomia"** ፡ ይወጣል ። ይህም ፥ ቃል ፡ በቃል ፦

- **"oiko"** ፤ ትዳር ፣ ማደሪያ ፣ ቤት ፣ ጎር ፣ አካባቢ ፤
- **"nomia"** ፤ ሕግ ፣ ሥርዐት ፣ ደንብ ፣ አስተዳደር ፣ አያያዝ ፤

በተገናኝ ፥ **"የትዳር ፡ አያያዝ"** ፡ *"መተዳደሪያ"* ፡ ወይም ፡ በግእዝ ፡ **"ምኅዳር"** ፣ **"ምስትኅዳር"** ፡ እንደ ፡ ማለት ፡ ነው ።

ቃሉ ፡ ባ 16 ኛው ፡ ምእትያ ፥ **የጥርየትኛ** ፡ ወይም ፡ የ economics ፡ አባት ፡ የተባለው ፡ ፈረንሳዊ ፡ ሊቅ ፡ ዠ፫ን ፡ ቦደ፫ ፡ - ፡ Jean ፡ Bodin ፡ (1522-1589 ፡ ዓ.ም. ፥ 1529-1596 ፡ A.D.) ፡ ከግሪክ ፡ ፈላስፎች ፡ ከክሴኖፎን ፡ - ፡ Xenophon ፡ እና ፡ ከአሪስጦጥል ፡ - ፡ Aristotle ፡ ሥራ ፡ የቀዳውና ፡ ያዋለው ፡ አባባል ፡ ነው ። ከዚያ ፡ ወዲህ ፡ በስኮቲሹ ፡ አዳም ፡ ስሚ፫ ፡ - ፡ Adam ፡ Smith ፡ (1715-1782 ፡ ዓ.ም. ፥ 1723-1790 ፡ A.D.) ፡ ፋና ፡ ወጊነት ፥ **ጥርየትኛ ፡ (economics)** ፡ ዐያሌ ፡ መራቀቅን ፡ ያየ ፣ ራሱን ፡ የቻለ ፡ የጥናትና ፡ የምርምር ፡ መስክ ፡ 'ኾኗል ። የዓለማችንን ፡ ታሪካዊና ፡ ወቅታዊ ፡ 'ኹኔታ ፡ የምንገመግምበት ፥ መጪውንም ፡ 'ኹኔታ ፡ የምንሸልግበት ፡ ወይም ፡ መላ ፡ የምንመታበት ፡ አንዱ ፡ መንገድ ፡ የጥርየትኛ ፡ መንገድ ፡ ነውና ፥ ኢትዮጵያና ፡ ሕዝቧ ፡ በዚህ ፡ የትንታኔ ፡ ዘርፍ ፡ እንድንጠቀምበት ፥ የጥርየትኛ ፡ ግሳችን ፡ አስቀድሞ ፡ እንዲሟላ ፡ ያሻል ። የዚህ ፡ ጽሑፍ ፡ ዋና ፡ ዐላማ ፡ ይህን ፡ ማስገንዘብ ፡ በመ'ኾኑ ፥ እጅግ ፡ ባጠረ ፡ መንገድ ፥ የጐደሉንን ፡ የጥርየትኛ ፡ ግሶች ፡ እንዴት ፡ ልናሟላቸው ፡ እንደምንችል ፡ ለማሳየት ፥ በጥቂት ፡ ቃላት ፡ ወይም ፡ ግሶች ፡ ተወስነን ፥ ዐማርኛውን ፡ ከግእዙ ፡ ጋራ ፡ ለጥቀን ፡ እንዘረዝራለን ።

### የግስ ፡ ርባታ ።

በተለይ ፡ ከግእዝና ፡ ካማርኛ ፡ የታደልናቸው ፡ የቋንቋዎቹ ፡ የመርባት ፡ ጠባዮች ፡ ሥራችንን ፡ በተወሰነ ፡ ደረጃ ፡ ያቃልሉልናል ። በግእዝና ፡ ባማርኛ ፥ ማንኛውም ፡ ቃል ፡ ከአንድ ፡ አንቀጽ ፡ ይረባል ፡ ወይም ፡ በርባታ ፡ ይገኛል ። ጥርየትኛን ፡ በተመለከተ ፥ ቀዳሚው ፡ ሥራ ፡ የጥናት ፡ ዘርፉን ፡ አንቀጽ ፡ ወይም ፡ መግቢያ ፡ ለይቶ ፡ ማግኘት ፡ ይ'ኾናል ። እላይ ፡ እንዳየነው ፥ ከ ፡ **"ኀደረ"** ፡ ተነሥተን ፡ **"ምኅዳር"** ፡ ወይም ፡ **"ምስትኅዳር"** ፡ እሚለው ፡ ቃል ፡ ላይ ፡ ደርሰናል ። ይህ ፡ ግን ፡ ደረቅ ፡ ትርጕሙ ፡ እንጂ ፥ ምስጢራዊ ፡ ትርጕሙ ፡ አይደለም ።

ምስጢራዊ ፡ ትርጕሙን ፡ ማግኘት ፡ የጕዳዩን ፡ ምንነት ፡ መመርመርን ፡ ይሻል ። ለዚህ ፡ እንዲረዳን ፥ አብዛኛው ፡ ምሁር ፡ ዘንድ ፡ ተቀባይነትን ፡ ያገኘውን ፡ የብሪታንያዊውን ፡ ዕውቅ ፡ **ጥርየተኛ** ፡ (economist) ፡ የላየነል ፡ ሮቢንዝ ፡ - ፡ Lionel Robbins ፡ (1892-1977 ፡ ዓ.ም. ፥ 1898-1984 ፡ A.D.) ፡ ድንጋጌን ፡ አንድ ፡ አፍታ ፡ እንመልከት ። ላየነል ፡ ሮቢንዝ ፡ "economics"ን ፦

> *በፍላጎቶችና ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ውለታ ፡ ወይም ፡ አዋዋል ፡ ባላቸው ፡ ውስኖች ፡ ዐቅሞች ፡ አንጻር ፡ ያለውን ፡ ሰብኣዊ ፡ አደራረግ ፡ ወይም ፡ ምርጫ ፡ የሚያጠና ፡ ጥበብ ።* [1]

ሲል ፡ አራቅቆ ፡ ይደነግገዋል ። በሌላ ፡ አነጋገር ፥ **ጥርየትኛ** ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ለኑሮው ፡ ምቾት ፡ ሲል ፥ ከምኅዳሩ ፡ ወይም ፡ ከማደሪያው ፡ የሚያገኛቸውን ፡ የተወሰኑ ፡ የተፈጥሮ ፡ ጸጋዎች ፡ ይዞ ፥ በተፈጥሮ ፡ በታደለው ፡ የመፍጠር ፣ የማቀድና ፡ የማቀናበር ፡ ችሎታዎቹ ፡ እየሠራ ፥ ያልነበረ ፡ ዐዲስ ፡ ሀብትን ፡ እያፈራና ፡ እየጠረየ ፡ (እየዋጀና ፡ እየሰጠ ፥ እየሸጠና ፡ እየለወጠ ፥ እየወረሰና ፡ እያወረሰ ፥ ወዘተ.) ፥ ልኮቻቸውና ፡ ዐይነቶቻቸው ፡ ላልተወሰኑ ፡ ፍላጎቶቹ ፡ ማርኪያ ፡ የሚያውልበትን ፡ አግባብ ፡ የሚመረምር ፡ ጥበብ ፡ ነው ። የሰው ፡ ልጅ ፡ 'ኹሉ ፥ በተፈጥሮው ፥ የሚራብ ፣ የሚጠማ ፥ የሚበርደው ፣ የሚሞቀው ፥ የሚታመም ፣ የሚሰበር ፥ የሚደክም ፣ ተመልሶም ፡ የሚበረታ ፥ የሚወለድ ፣ የሚሞት ፥ ደማዊ ፡ ፍጥረት ፡ ነውና ፥ ለኑሮው ፡ ድሎትን ፡ ሲሻ ፥ ከማደሪያው ፡ በሚያገ'ኘው ፡ ዐላቂና ፡ ውስን ፡ ዐቅም ፡ ሰብኣውያን ፡ ፍላጎቶቹን ፡ መርጦ ፡ ያረካል ። ይህ ፡ የሰዎች ፡ ጥርየታዊ ፡ ሱታፌ ፡ የሚካ'ኼድበት ፡ ቦታም ፣ ጊዜም ፣ ሥርዐትም ፡ **ምጥራይ** ፡

---

1 *"**Economics** is the science which studies human behaviour as a relationship between ends and scarce means which have alternative uses."* **Lionel Robbins**, *Essay on the Nature and Significance of Economic Science*, MacMillan & Co., London, 1932 A.D., p.15.


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።

(economic system | système économique) ፡ ይባላል ።

በግእዝ ፥ አንቀጹ ፡ "ጠረየ" ፡ ነው ፤ ይህም ፡ ጥሪትን ፡ አጠራ/አጠረየ ፣ ገንዘብን ፡ አገኘ ፣ ሰበሰበ ፥ የሌላውን ፡ ጥሪት ፡ ዋጀ ፣ ገዛ ፣ ገንዘብ ፡ አደረገ ፣ ወረሰ ፣ አወረሰ ፣ ሰጠ ፡ ማለት ፡ ነው ።

በርባታ ፡ ዝርዝሩ ፡ ያየነው ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡—

| | ግእዝ | ዐማርኛ | እንግሊዝኛ | ፈረንሳይኛ |
|---|---|---|---|---|
| አርእስት | ጠርዩ/ጠርዮት | መጠረት | to economize | économiser |
| ቀዳማይ | ጠርየ/ጠረየ | ጠረየ | economize | économise |
| ሣልስ ፡ ቅጽል | ጠራዪ | ጠራዪ | economic agent | agent économique |
| ሳድስ ፡ ቅጽል | ጥሩይ | ጥርይ/ጥሬ | value | valeur |
| መስም ፡ ቅጽል | መጥረዪ | መጥሪ/ት | value creator | créateur de valeur |
| ሳቢ ፡ ዘር | ጥርየት | አጠራረይ | economy | économie |
| ባዕድ ፡ ዘር | ምጥራይ | መጥረያ | economic system | système économique |
| ምዕላድ | ጥሪት | ጥሪት | wealth | richesse |
| ባዕድ ፡ ከምዕላድ | መጥሪት | መጥሪት | capital | capital |

ግእዝና ፡ ዐማርኛ ፡ ተለያይተው ፡ ያልተለያዩ ፡ ቋንቋዎች ፡ ናቸውና ፥ ያማርኛው ፡ ቃል ፡ አሻሚ ፡ ሲመስለን ፥ የግእዙን ፡ መያዝ ፡ ተለምዷል ። በጥርየትኛ [2] ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፥ በሌላውም ፡ የጥናት ፡ መስክ ፥ ተፈላጊ ፡ በኾነበት ፡ ጊዜና ፡ ኹኔታ ፡ ኹሉ ፥ የግእዝ ፡ ቃልን ፡ መምረጡ ፡ ይደገፋል ፤ እንዲያውም ፡ ብዙ ፡ ጥቅም ፡ ይኖረዋል ። የቃላቱ ፡ ፍች ፡ በግእዝ ፡ መዝገበ ፡ ቃላት ፡ ተሟልቶ ፡ ስለሚገኝ ፥ ይህ ፡ አደራረግ ፡ የጥናትንና ፡ የምርምርን ፡ አድማስ ፡ የሚያሰፋ ፡ እንጂ ፡ የሚያጠብ ፡ አይኾንም ።

ከዚህ ፡ ኹሉ ፡ በላይ ፡ ደግሞ ፥ የጥናት ፡ መስኩ ፡ በጠቅላላው ፡ ካንድ ፡ አንቀጽ ፡ በሚረቡ ፡ ቃላት ፥ ምትና ፡ ግቱ ፣ መነሻና ፡ መድረሻው ፡ ስለሚገኝልን ፥ ታላቅ ፡ ርዳታን ፡ በነጻ ፡ እናገኛለን ። ፈረንጅኛው ፡ economize ፣ economic ፣ economic agent ፣ economic system ፣ value ፣ good ፣ capital ፣ wealth ፡ እያለ ፡ ካንድ ፡ ዘር ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ዘር ፣ ካንድ ፡ አንቀጽ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አንቀጽ ፡ ሲዘል ፥ ግእዝ–ዐማርኛችን ፡ ኹሉንም ፡ ግሶች ፡ ከዚያው ፡ ከ"ጠረየ" ፡ ዘር ፡ አርብቶ ፡ ይሰጠናል ። የእኛ ፡ ፈንታ ፡ ተገቢውን ፡ ትርጕም ፡ ለያንዳንዱ ፡ ግስ ፡ መስጠት ፡ ይኾናል ። ይህ ፡ በ"ጠረየ" ፡ ያየነው ፡ ድንቅ ፡ ችሎታ ፡ ለማንኛውም ፡ ሌላ ፡ የጥናት ፡ መስክ ፡ ይውላልና ፥ ሊቆቻችን ፡ በየሚያ ፡ መስካቸው ፡ ምርምራቸውን ፡ በግእዝ–ዐማርኛ ፡ እያራቀቁ ፥ ዕውቀትን ፡ በቋንቋችን ፡ እንዲያጐናፍሩልን ፡ ከንግዲህ ፡ ልንለምናቸው ፡ አይገባም ። *"ለብልኽ ፡ አይነግሩ ፤ ላንበሳ ፡ አይመትሩ..."*

ስለ ፡ ጥርየታዊ ፡ ትንታኔ ፥ ባለፉት ፡ 300 ፡ ዓመታት ፡ ዐያሌ ፡ የስልት ፡ መራቀቆች ፡ ታይተዋል ። ከፊሉ ፡ በተለያዩ ፡ የጎሊኛ ፡ (የ ideology | የ idéologie) ፡ ጐራዎች ፡ ሲመሸጉ ፥ ከፊሉ ፡ ደግሞ ፡ በስልትና ፡ በቀረባ ፡ ብቻ ፡ ተለያይተው ፡ ይወዳደራሉ ። አንድጋ ፡ ሲታዩ ፡ ደግሞ ፥ ለጥናት ፡ መስኩ ፡ ብዙ ፡ ማማረጫዎችን ፡ ይሰጣሉ ። በዚህ ፡ ረገድ ፥ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ይህ ፡ ነው ፡ የሚባል ፡ ያበረከትነው ፡ ስልትም ፡ ኾነ ፡ ቀረባ ፡ ስለሌለ ፥ *"ኢትዮጵያዊ ፡ ጥርየታዊ ፡ ትንታኔ"* ፡ ብለን ፡ የምናሳየው ፡ የለንም ፤ በጕዳዩ ፡ ገና ፡ ተማሪዎች ፡ ነን ። ግእዝ–ዐማርኛ ፡ የሚሰጠንን ፡ የቋንቋ ፡ ኀይል ፡ ባግባቡ ፡ ብንሠራበትና ፥ ከርትዕ ፡ ሥልጣኔያችን ፡ መሠረት ፡ ብንነሣ ፥ ዝግየታችንን ፡ ባጪር ፡ ጊዜ ፡ እናስወግደዋለን ❖

2 *"Economy"*ን ፡ ለመዠመሪያ ፡ ጊዜ ፡ *"ጥርየት"* ፡ ብለው ፡ በጽሑፍ ፡ የተረጐሙት ፡ ሊ.. ፡ ዤኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ነበሩ ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2011 ፡ ዓ.ም. ።